**የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)**

***Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)***

(ዴሞክራሲያዊ/Democratic)

ጥር ፴ ቀን ፪ ሺህ ፯ ዓ. ም
February 7, 2015

# ከአምባገነኖች ሽብር እንጂ ዴሞክራሲ አይጠበቅም!

አምባገነኖች በታሪካቸው ሕዝብን ይፈራሉ፤ ሥልጣናቸውን በእጃቸው ለማቆየት ሲሉም ሌሎች አቻዎቻቸው የሄዱበትን ፀረ-ሕዝብ መንገድ ሁሉ ይከተላሉ። በእስያ፣ በምሥራቅ አውሮጳ፣ በአፍሪቃና በላቲን አሜሪካ ሀገሮች ወደ ሥልጣን የመጡ አምባገነኖች ሁሉ በሕዝብ ተገፍተው ከሥልጣናቸው እስኪወገዱ ድረስ፣ ከእነሱ ሀሳብና መስመር የተለዩትን ሁሉ እያሰሩ፣ እያሰቃዩና እየገደሉ ነበር እስከ ሥልጣናቸው መጨረሻ የዘለቁት።

በአገራችንም፣ ይህ በሕዝባችን ጫንቃ ላይ በጠመንጃ አፈሙዝ ተፈናጦ፣ በፍርሃት እየተርበደበደ ያለው የህወሓት/ኢሕአዴግ አምባገነን አገዛዝ፣ እንደሌሎች አቻዎቹ ሁሉ ሥልጣን ላይ ከመውጣቱ በፊት ጀምሮ ከራሱ አስተሳሰብ ጋር የማይሄዱትን ሲያስርና ሲገድል ቆይቷል። ሥልጣን ላይ ከወጣ በኋላም፣ የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎችን፣ ጋዜጠኞችንና ግለሰቦችን አስሯል፤ ገድሏል፤ ከአገር እንዲሰደዱም አድርጓል። በራሱ ሳምባ የሚተነፍሱ የድርጅት አመራሮችን ሳይቀር እንኳን ገድሏል፤ ከሥራ አባሯል፤ በሌሎች ድርጅቶች ስም ለራሱ የሚያገለግሉ የካድሬዎች ጥርቅም ድርጅትም ፈጥሯል። ለምሳሌ በቅንጅት ስም ሌላ ተለጣፊ ድርጅት ፈጥሮ መገልገያ መሳሪያው ማድረጉ የቅርብ ትውስታችን ነው።

እራሱ ጻፍሁት በሚለው ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 30 በነፃ የመደራጀትና ሐሳብን የመግለጽ መብት ለሁሉም ዜጎች እንደሚፈቅድ እየገለጸ፣ ይህንኑ አንቀጽ ቀድሞ የሚሽረው ግን እራሱ አምባገነኑ የህወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ነው።


**P.O.Box 8141**
**Silver Spring, MD 20910**

**P.O.Box 88675**
**Los Angeles, CA 90009**

**Phone: 202- 241 2078**

**Email Address: eprp-democratic@eprp-ihapa.com**

ቀደም ሲል እንዳደረገው ሁሉ፣ ሕገ-መንግሥታዊ መብታችን ነው ብለው በባዶ እጃቸው ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ የወጡትን ዜጎች ሁሉ በጠራራ ፀሐይ በቅልብ ወታደሮቹ አስደብደቧል፤ አስሯል። ይህ አምባገነን አገዛዝ በዚህ ድርጊት ሳያበቃም፣ አሁን በቅርቡ በሕጋዊነት በሚንቀሳቀሰው የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት ስም በራሱ ሳንባ የሚተነፍሱ ግለሰቦችን አሰባስቦ፣ እሱን መሳይ ድርጅት በመፍጠር፣ ሕጋዊውን የአንድነት ድርጅት አፍርሷል።

ይህ ድርጊቱ፣ ሕዝብን አምርሮ እንዲነሳሳ የሚገፋፋ እንጂ፣ እሰየው አበጀህ የሚያስብል ድጋፍ የሚያስቸረው ድርጊት አልሆነለትም። ይልቁንም፣ ይህንን እልህ አስጨራሽ ትግል በድል አድራጊነት ለመወጣት፣ በሺህ የሚቆጠሩ ዜጎች ትግሉን እንዲቀላቀሉ የሚጋብዝ እንጂ ተስፋ አስቆራጭ ድርጊት ከቶውንም ሊሆን አይችልም። ማንኛውም አገር ወዳድ ሁሉ ይህንን በትዕቢት የተወጠረ የማናለብኝነት እርምጃ ሊያወግዘውና በቁርጠኝነት ሊታገለው የሚገባ ዓብይ ብሔራዊ ጉዳይ ነው።

በዚህ አጋጣሚ ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) በአደባባይ ለተደበደቡ፣ ለቆሰሉና ወደ እስርቤት ለታጎሩ ሁሉ ትግላችሁ ትግላችን እንደሆነ እያረጋገጠ፣ ይህንን ክቡር ዓላማ ከግቡ ለማድረስ በቁርጠኝነት ከጎናችሁ ቆሞ እንደሚፋለም ያስገነዝባል። የኅብረት ተጋድሏችን በቅርቡ ፍሬ ሊያፈራ እንደሚችል እርግጠኞች በመሆንም፣ ተቃዋሚ ኃይሎች ሁሉ ለዚህ ጥረት እንዲተባበሩ አሁንም ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ደግሞ ደጋግሞ ጥሪውን ያስተጋባል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቸንፋል!!